# የግል ድርጅት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ፈንድ አስተዳደር

## በፕሮቪደንት ፈንድ ወይም በሌላ ስያሜ በሚጠራ ዐቅድ ተጠቃሚ የነበሩ ሠራተኞች በግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ ስለሚሸፈኑበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 02/2014

ነሃሴ 2014 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## ማውጫ


1 መግቢያ ........................................................................ 2

2 አጭር ርዕስ ........................................................................ 2

3 ትርጓሜ ........................................................................ 2

4 ዓላማ ........................................................................ 1

5 የተፈጻሚነት ወሰን ........................................................................ 2

6 በግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ ስለመሸፈን ........................................................................ 3

7 ስለ አገልግሎት ዘመን አያያዝ ........................................................................ 3

8 የማስረጃዎች አቀራረብ ........................................................................ 5

9 የፕሮቪደንት ፈንድ ወይም የዐቅድ ገንዘብ ገቢ አደራረግ ........................................................................ 6

10 የፕሮቪደንት ፈንድ ወይም ዐቅድ ገንዘብ ገቢ እንዲደረግ ስለሚሠጥ ውሳኔ ................ 6

11 የአሠሪው የግል ድርጅት ግዴታ ........................................................................ 6

12 የመሸጋገሪያ ድንጋጌ ........................................................................ 6

13 መመሪያውን ስለማሻሻል ........................................................................ 6

14 የመመሪያው ተፈጻሚነት ........................................................................ 7

## መግቢያ

በፕሮቪደንት ፈንድ ወይም በሌላ ስያሜ በሚጠራ ዐቅድ ተጠቃሚ የነበሩ ሠራተኞች በግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ ስለሚሸፈኑበት ሁኔታ ለመወሠን መመሪያ ማውጣት በማስፈለጉ፣

የግል ድርጅት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ፈንድ አስተዳደር በግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 1268/2014 አንጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2 እና አንቀጽ 59 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሠጠው ስልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

### 1 አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በፕሮቪደንት ፈንድ ወይም በሌላ ስያሜ በሚጠራ ዐቅድ ተጠቃሚ የነበሩ ሠራተኞች በግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ ስለሚሸፈኑበት ሁኔታ ለመወሠን የወጣ መመሪያ ቁጥር 02/2014"ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጓሜ የሚያሠጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "አዋጅ" ማለት የግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 1268/2014 ነው።
2. "የፕሮቪደንት ፈንድ" ማለት በሠራተኛው መደበኛ የወር ደመወዝ ላይ ተመስርቶ በየወሩ ከሠራተኛው ደመወዝ ላይ ተቀንሶ እና የአሰሪው ድርሻ ተጨምሮ ወይም በግል ድርጅቱ ብቻ በሚደረግ መዋጮ በግል ድርጅቱ የባንክ ሂሳብ ወይ በሠራተኛው ስም በተከፈተ የባንክ ሂሳብ የሚጠራቀም ገንዘብ ነው።
3. "በሌላ ስያሜ የሚጠራ ዐቅድ" ማለት የማህበራዊ ዋስትና አሠራርን ተከትሎ በአሠሪው የግል ድርጅት እና በሠራተኛው ወይም በአሠሪው የግል ድርጅት የተቋቋመ ዐቅድ ነው።
4. "አስተዳደር" ማለት የግል ድርጅት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ፈንድ አስተዳደር ሲሆን የአስተዳደሩን ሪጅን እና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ይጨምራል።

### 3. ዓላማ

ይህ መመሪያ ጸንቶ በስራ ላይ ከመዋሉ አስቀድሞ በግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ ያልተሸፈኑ የግል ድርጅት ሠራተኞች በግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ የሚሸፈኑበት እና የተጠራቀመ የፕሮቪደንት ፈንድ ገንዘብ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ በማድረግ

ቀደም ሲል የፈጸሙት አገልግሎት ለጡረታ አበል አወሳሰን የሚታሰብበትን ሁኔታ መወሠን ነው፡፡

4. **ተፈጻሚነት**

4.1. ይህ መመሪያ ከሃምሌ 2003 ዓ.ም በፊት በተቋቋመ የግል ድርጅት በነበራቸው ፕሮቪደንት ፈንድ ወይም በሌላ ስያሜ በሚጠራ የማህበራዊ ዋስትና ዐቅድ ተጠቃሚነታቸውን ለመቀጠል ወስነው የቀጠሉና በግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ ያልተሸፈኑ የግል ድርጅት ሠራተኞች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4.2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4.1 ድንጋጌ እድሜያቸው ከመስከረም 1 ቀን 2015 ዓ.ም አስቀድሞ ዕድሜያቸው 60 በሞላ የግል ድርጅት ሠራተኞች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

5. **በግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ ስለመሸፈን**

በአዋጁ አንጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ከሃምሌ 2003 ዓ.ም በፊት በተቋቋመ የግል ድርጅት በነበራቸው ፕሮቪደንት ፈንድ ወይም በሌላ ስያሜ በሚጠራ ዐቅድ ተጠቃሚነታቸውን ለመቀጠል ወስነው የቀጠሉና በግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ ያልተሸፈኑ የግል ድርጅት ሠራተኞች በአጠቃላይ ከመስከረም 1 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ በግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ ይሸፈናሉ፡፡

6. **ስለ አገልግሎት ዘመን አያያዝ**

6.1. በአዋጁ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2 እና በዚህ መመሪያ መሰረት በግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ ለሚሸፈን የግል ድርጅት ሠራተኛ አገልግሎቱ ለጡረታ አበል አወሳሰን መታሰብ የሚጀምረው በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በጡረታ ዐቅድ ከተሸፈነበት ከመስከረም 1 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ነው፡፡

6.2. የግል ድርጅት ሠራተኛው ይህ መመሪያ ጸንቶ በስራ ላይ ከመዋሉ አስቀድሞ የተጠራቀመ የፕሮቪደንት ፈንድ ወይም ዐቅድ ገንዘቡ ለግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ ገቢ እንዲደረግለት በማድረግ አገልግሎቱ ለጡረታ አበል አወሳሰን እንዲታሰብለት ማድረግ ይችላል፡፡

6.3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6.1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በፕሮቪደንት ፈንድ ወይም በሌላ ስያሜ የሚጠራ የዐቅድ ገንዘቡን ለግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ ገቢ አድርጎ ይህ መመሪያ ጸንቶ በስራ ላይ ከመዋሉ አስቀድሞ የፈጸመው አገልግሎቱ ለጡረታ አበል አወሳሰን እንዲታሠብለት በጽሁፍ በማመልከቻ ለሚጠይቅ የግል ድርጅት ሠራተኛ ገንዘቡ ለግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ

ገቢ ሲደረግ ከመስከረም 1 ቀን 2015 ዓ.ም በፊት ጀምሮ ወደ ሁዋላ ሲከፈለው በነበረው የደመወዝ መጠን ልክ ሊከፈል የሚገባውን 18 % የጡረታ መዋጮ በሸፈነው መጠን አገልግሎቱ ለጡረታ አበል አወሳሰን ይታሰብለታል።

6.4. በዚህ መመሪያ መሠረት በግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ ለሚሸፈን የግል ድርጅት ሠራተኛ ከመስከረም 1 ቀን 2015 ዓ.ም አስቀድሞ የፈጸመው አገልግሎቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6.3 መሠረት ለጡረታ አበል አወሳሰን ሊታሠብ የሚችለው ይህ መመሪያ ጸንቶ በስራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ በ 6 ወር ጊዜ ውስጥ የፕሮቪደንት ፈንድ ወይም በሌላ ስያሜ የሚጠራ ዐቅድ ገንዘቡ ለግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ ገቢ የተደረገ እንደሆነ ብቻ ነው።

## 7. ለአገልግሎት ዘመን አያያዝ ስለሚቀርቡ ማስረጃዎች

7.1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6.3 መሠረት በፕሮቪደንት ፈንድ ወይም በሌላ ስያሜ በሚጠራ ዐቅድ የተጠራቀመ ገንዘብ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ተደርጎ ከመስከረም 1 ቀን 2015 ዓ.ም በፊት የፈጸመው አገልግሎት ለጡረታ አበል አወሳሰን እንዲታሰብለት በጽሁፍ ማመልከቻ የሚጠይቅ የግል ድርጅት ሠራተኛ በየወሩ ሲከፈለው የነበረውን ደመወዝ የሚያሳዩ የደመወዝ ክፍያ ወይም ጭማሪ እና የሠራተኛው ማመልከቻ ከዋናው ጋር የተገናዘቡ ፎቶ ኮፒ ማስረጃዎች፣በዚህ መመሪያ አባሪ 1 ላይ የተመለከተው ሠንጠረዥ ሠራተኛው ያለው የፕሮቪደንት ፈንድ ወይም በሌላ ስያሜ የሚጠራ ዐቅድ የገንዘብ መጠን ጨምሮ ሌሎች መረጃዎቹ በዝርዝር ተሞልተው እና በሚመለከተው የስራ ኃላፊ ተረጋግጠው ለአስተዳደሩ መቅረብ አለባቸው።

7.2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7.1 እና አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ መሠረት የተመለከተው አጠቃላይ የጡረታ መዋጮ ገቢ ድምር እና ለጡረታ ፈንዱ ገቢ የሚደረገው የፕሮቪደንት ፈንድ ወይም በሌላ ስያሜ የሚጠራ ዐቅድ የተጠራቀመ ገንዘብ መጠን ተመሳሳይ መሆን አለበት።

7.3. የግል ድርጅት ሠራተኛው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7.1 የተጠቀሱትን ማስረጃዎች ለአስተዳደሩ እንዲያቀርብለት ለሚሠራበት የግል ድርጅት በማመልከቻ ሲጠይቅ ማመልከቻው በቀረበ በ 60 ተከታታይ ቀን ውስጥ የግል ድርጅቱ ማስረጃዎቹን አሟልቶ ለአስተዳደሩ የመላክ ግዴታ አለበት።

7.4. የግል ድርጅት ሠራተኛው የፕሮቪደንት ፈንድ ገንዘቡ ገቢ ተደርጎ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6.2 መሠረት አገልግሎቱ ለጡረታ አበል አወሳሰን እንዲታሠብለት ለግል ድርጅቱ ማመልከቱ ወይም ማስረጃው ለአስተዳሩ መቅረቡ ከተረጋገጠ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 6.4 የተጠቀሠው የጊዜ ገደብ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

## 8. የፕሮቪደንት ፈንድ ወይም የዐቅድ ገንዘብ ገቢ እንዲደረግ ስለሚሠጥ ውሳኔ

8.1. የፕሮቪደንት ፈንድ ወይም የዐቅድ ገንዘብ ገቢ ተደርጎ አገልግሎቱ ለጡረታ አበል አወሳሰን እንዲታሠብ ውሳኔ የሚሠጠው በአስተዳደሩ ነው፡፡

8.2. አስተዳደሩ የፕሮቪደንት ፈንድ ወይም በሌላ ስያሜ የሚጠራ የዐቅድ ገንዘብ ገቢ እንዲደረግ የሚወሰነው የግል ድርጅት ሠራተኛው በግል ድርጅት ሠራኞች ጡረታ ዐቅድ ከተሸፈነበት ወር አስቀድሞ ባሉት ጊዜያት በየወሩ የተከፈለውን ደመወዝ መሠረት አድርጎ በየወሩ ሊከፈል የሚገባውን 18% የጡረታ መዋጮ በማስላት ነው፡፡

## 9. ውሳኔ ስለማሳወቅ

9.1. የግል ድርጅት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ፈንድ አስተዳደር ውሳኔውን የሚያሳውቀው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 8.2 ከተጠቀሠው የገንዘብ መጠን በተጨማሪ የፕሮቪደንት ፈንድ ወይም በሌላ ስያሜ የሚጠራው ዐቅድ ለሠራተኛው የሸፈነውን የአገልግሎት ዘመን ብዛት እና ከመቼ ጀምሮ ያለው አገልግሎቱ ለጡረታ አበል አወሳሰን እንደታሰበለት እንዲሁም ገንዘቡ ገቢ የሚደረግበት የባንክ ሂሳብ ቁጥር በአድራሻ ለአሠሪው የግል ድርጅት እንዲሁም በቅጂ ለሠራተኛው እንዲያውቀው በማድረግ ነው፡፡

9.2. አሠሪው የግል ድርጅት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9.1 መሠረት የሠራተኛው የፕሮቪደንት ፈንድ ወይም በሌላ ስያሜ የሚጠራ ዐቅድ ገንዘብ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ እንዲደረግ ደብዳቤ ከደረሠው ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ውስጥ ገቢ አድርጎ ማስረጃ ካላቀረበ በግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 1268/2014 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት ወለድና ቅጣት የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

9.3. አስተዳደሩ የፕሮቪደንት ፈንድ ወይም የዐቅድ ገንዘብ ገቢ እንዲደረግ የሚወስነው የግል ድርጅት ሠራተኛው በዚህ መመሪያ መሠረት በግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ ከመሸፈኑ አስቀድሞ ዕድሜ(60) ያላላፈ መሆኑ በዚህ መመሪያ



የግል ድርጅት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ

አንቀጽ 11 መሠረት ተደራጅቶ ከቀረበው የምዝገባ ማስረጃ ወይም ማህደር በማጣራትና በማረጋገጥ ነው፡፡

**10.የፕሮቪደንት ፈንድ ወይም የዐቅድ ገንዘብ በሠራተኛው ስም ገቢ ስለመደረጉ**

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 እና 9 መሠረት ከመስከረም 1 ቀን 2015 ዓ.ም በፊት የተፈጸመን አገልግሎት ለማስያዝ የፕሮቪደንት ፈንድ ወይም የዐቅድ ገንዘብ ገቢ የሚደረገው የፕሮቪደንት ፈንድ ወይም የዐቅድ ገንዘቡ ገቢ ተደርጎ ቀደም ሲል የፈጸመው አገልግሎቱ ለጡረታ አበል አወሳሰን በሚታሰብለት ሠራተኛ ስም ነው፡፡

**11. የማስረጃዎች አደረጃጀት**

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 መሠረት የፕሮቪደንት ፈንድ ወይም የዐቅድ ገንዘብ ገቢ የተደረገበት ማስረጃ በአንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 8.2 እና 8.3 መሠረት የተሰላው የፕሮቪደንት ፈንድ ወይም ዐቅድ ገንዘብ ገቢ መጠን ዝርዝርና ማሳወቂያ ደብዳቤ ተደራጅቶ የሚያያዘው በአስተዳደሩ ተደራጅቶ በተያዘው የአሠሪው እና የሠራተኛው የምዝገባ ማህደር ውስጥ ነው፡፡

**12. የአሠሪው የግል ድርጅት ግዴታ**

12.1. በአዋጁ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሠረት ይህ መመሪያ ጸንቶ በስራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ በ60 ቀናት ውስጥ በአዋጁ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2 እና በዚህ መመሪያ መሠረት በግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ የተሸፈኑትን የግል ድርጅቱን ሠራተኞች ዝርዝር፣ ሠራተኛው ለመጀመሪያ ግዜ ሲቀጠር በቅድሚያ የመዘገበውን የልደት ዘመን የሚያሳይ ማስረጃ፣ ስርዝ ድልዝ የሌለበት የግል የቤተሠብና የአገልግሎት ሁኔታ መግለጫ ቅጽ(ቅፅ ጡ1)፣የቅጥር ደብዳቤ/የስራ ውል፣ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7.1 የተመለከቱትን ማስረጃዎች አሟልቶ በሸኚ ደብዳቤ ለአስተዳሩ ለምዝገባ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

12.2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 12.1 መሰረት የሰራተኛው ማስረጃ ተሟልቶ ሲቀርብ በአዋጁ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ለግል ድርጅት ሠራተኛው የማህበራዊ ዋስትና መለያ ቁጥር ይሠጣል፡፡

**13. ቅጣት**

በዚህ መመሪያ መሠረት የተጣለበትን ግዴታ ያልተወጣ የግል ድርጅት ወይም የሚመለከተው የስራ ኃላፊ በግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 1268/2014 አንቀጽ 61 መሠረት በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 14. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህን መመሪያ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በግል ድርጅት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ፈንድ አስተዳደር የስራ አመራር ቦርድ ሊሻሻል ይችላል፡፡

## 15. ተፈጻሚነት

ይህ መመሪያ ከመስከረም 1 ቀን 2015 ዓ.ም. ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡

ተክለወልድ አጥናፉ

በሚኒስትር ማዕረግ የጠቅላይ ሚኒስትር

ሲኒየር የማክሮ ኢኮኖሚ አማካሪና

በግል ድርጅቶች ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስት ፈንድ አስተዳደር

የስራ አመራር ቦርድ ሠብሳቢ

አባሪ 1

## የፕሮቪደንት ፈንድ ገንዘብ ገቢ በማድረግ ቀደም ሲል የተፈጸመ አገልግሎቱ ለጡረታ አበል አወሳሰን እንዲታሰብ ለቀረበ ጥያቄ የሠራኛውን ዝርዝር መረጃ መስጫ ቅጽ

የድርጅቱ ስም-------------------------------------------------

የድርጅቱ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር------------------------------------------------

የሠራተኛው ሙሉ ስም እስከ አያት ------------------------------------------------------------------------

በድርጅቱ የተቀጠረበት ወር፣ቀን፣ዓ፣ም------------------------------------------------------

የተጠራቀመ የፕሮቪደንት ፈንድ ገንዘብ መጠን-ብር በአሃዝ--------------------በፊደል ------------------

የአቶ/ወ/ሮ----------------------------------------------------ከ---------------------------------------ዓ.ም ጀምሮ
የደመወዝ ክፍያ ዝርዝር

| ተ.ቁ | የደመወዝ ክፍያ | | የወራት ብዛት | ደመወዝ | ወራት ብዛት ሲባዛ በደመወዝ | ሊከፈል የሚገባው18% የጡረታ መዋጮ በ ብር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከ | እስከ | | | | |
| 1 | | | | | | |
| 2 | | | | | | |
| 3 | | | | | | |
| 4 | | | | | | |
| 5 | | | | | | |
| 6 | | | | | | |
| 7 | | | | | | |
| 8 | | | | | | |
| 9 | | | | | | |
| 10 | | | | | | |
| | ድምር | | | | | |

**ያዘጋጀው የስራ ኃላፊ**

ሙሉ ስም-----------------------------------------

ፊርማ-----------------------------------------------

ቀን----------------------------------------------------

**ያረጋገጠው የስራ ኃላፊ**

ሙሉ ስም-----------------------------------------

ፊርማ-----------------------------------------------

ቀን----------------------------------------------------

የድርጅቱ ክብ ማህተም::